# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

28

★ አብዮታችን ይግፋ

★ አብዮትና ወጣቱ

★ የቬትናም ሠራተኞች ፓርቲ ዋና ጸሐፊ

★ የቅራኔ ገጽታዎች አንድነትና ትግል

ሰኔ ፲፭ — ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# አብዮታችን ይግፋ !

የኢትዮጵያ አብዮት ሒደት እጅግ ከመፍጠኑ የተነሣ ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ አቋሞችን፤ የመደብ ይዘታቸውን ፤ በአብዮቱ ላይ ወይም ለአብዮቱ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤቶች ቆም ብሎ ለመመርመር ፤ ለመከራከርና በቅድሚያ ይኸኛው መሥመር ያዋጣል እየተባለ ተከትሎ ለመጓዝ ብዙም ፋታ የተገኘበት አብዮት አይደለም ። ይህም ሆኖ ፤ ምንም እንኳን በወዝአደር ፓርቲና እሱም ሊደስገኘው በሚችለው ጥራት ያለው ግንባር ቀደም የፖለቲካ መሥመር ባይመራም ፤ እስካሁን ድረስ በሐቀኛ አብዮታውያን ከፍተኛ ተጋድሎ የተሳሳቱ መሥመሮችን ወደጐን እየተወ ያለማቋረጥ ወደፊት በመገሥገሥ ላይ ነው ።

በዚህ አንፃር እስካሁን አብዮታችንን ገደል ሊከቱ ይችሉ የነበሩ ብዙ የተሳሳቱ ተራማጅ መሳይ ግን አድኃሪ መሥመሮች እየተጋለጡ መጥተዋል ። «የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መፈክር መሸነፍና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቃ ፤ በተደራጀ ፤ በታጠቀ ሕዝብ ዓመፅ መፈክር ሥር ከዳር እስከ ዳር መሠለፉ ለዚህ አንድ ምስክር ነው ። ሌሎችም ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን እንደዋና ጠላት አድርገው ይቆጥሩ የነበሩ አድኃሪ አስተሳሰቦች ፤ ዲሞክራሲ ለጠቅላላው ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ይለቀቁ ይሉ የነበሩ የአድኃሪዎች መፈክሮች . . . . ወዘተ እንዲሁ በሁለት መሥመር ትግል እየተሸነፉና እየተጋለጡ ዛሬ በነዚህ ጥያቄዎች ላይ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥራት ያለውን አብዮታዊ መሥመር እየተከተለ ትግሉን በማፋፋም ላይ ነው ።

ወይም መደቦች እስካሉ ድረስ ፤ እንኳን በአብዮት ትግል ወቅት ይቅርና አብዮት ድል አድርጎ በተደላደለባቸው አገሮች እንኳን ቢሆን ፤ ሁልጊዜ የመሥመር ትግል አለ ። እንኳን ገና ተሸንፈው ሳያልቅላቸው ይቅርና የወዝአደሩ የበላይ ገዢነት በመቃብራቸው ላይ ከተመሠረተ በኋላ እንኳን አድኃሪዎች ለማንሠራራትና የቀድሞውን እንደነበረ ለመመለስ የሚያደርጉትን ትግል በምንም ዓይነት አያቆሙም ። ለምሳሌ ወደ ቻይና ብንሔድ ፤ አብዮቱ አንድ የድል ምዕራፍ ተቀዳጅቶ ወዝአደሩ ሥልጣን ከያዘ ከ፳፰ ዓመት በኋላ ፤ በዛሬው ወቅት ፤ በዚች አገር ከፍተኛ የመደቦች ትንቅንቅ ከፍተኛ የሁለት መሥመር ትግል ሲካሔድ እናያለን ።

ዛሬም በአገራችን ይኸው ነው ። በአብዮትና በፀረ አብዮት መካከል የሚደረገው ትግል በልዩ ልዩ መልክና በልዩ ልዩ ደረጃዎች ተፋፍሞ በመካሔድ ላይ ይገኛል ። ከዚህም ጋር ተያይዞ የመሥመር ትግል አለ ። በተለያዩ አዝማሚያዎች መሐከል የሚደረገው የመሥመር ትግል ብዙውን ጊዜ የሚያተኩረው ፤ ከአንድ ከተወሰነ ተጨባጭ ሁኔታ ተነሥቶ አብዮቱ መከተል ያለበት ፋና የትኛው ነው ? በሚለው ጥያቄ ላይ ሊሆን ይችላል ።

በዛሬው ወቅት አገራችን በአብዮቷና በአንድነቷ ጠላቶች መከበቧን የሚክድ የለም ። በዛሬው ወቅት አገራችን አብዮቷን ፤ ብሔራዊ ክብሯንና አንድነቷን ለመጠበቅ እነዚህን ጠላቶቿን ሁሉ መደምሰስ እንዳለባት የማይቀበል የለም ። ልዩነትና ክርክር ሊመጣ የሚችለው ፤ እነዚህን ጠላቶች እንዴት አድርገን ደምስሰን አብዮታችንን ፈር እናስይዝ ፤ አንድነታችንና የእናት አገራችንን ክብርና ህልውና እናስከብር በሚለው ጥያቄ ነው ።

አብዮታውያን ደግመው ደጋግመው እንዳበሠሩት ፤ ዛሬ አገራችንን ከየአቅጣጫው ቀስፈው የያዟት ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት ፤ በአብዮቱ መግፋት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ ። ይህ ቀላል አነጋገር ፤ ሁሉም ሰው የሚቀበለው አነጋገር ይመስላል ። ነገር ግን ይህንን ቀላል አነጋገር ሁሉም ሰው ተቀብሎታል ማለት አይቻልም ። ለምሳሌ የነዓለማየሁ ኃይሌ «መሥመር» ፤ «ዛሬ አገራችን በብዙ ችግሮች ተወጥራ ስለተያዘች የውስጡን ትግል አቀዝቅዘን ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነን የውጭ ጠላቶቻችንን እንደምስስ» የሚል ለአብዮቱ ያሰበ የሚመስል ግን ፀረ—አብዮት የሆነ መሥመር ያስተጋቡ ነበር ። ይኸ መሥመር ዞሮ ዞሮ አብዮታችንን ለጊዜው «ተወት»አድርገን በእናት አገራችን ላይ የተነሡትን ጠላቶች እንቋቋም የሚል መሥመር ነበር ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ፤ የውስጥና የውጭ ጠላቶቹን በምንም ዓይነት ለይቼ አላያቸውም በማለት «የውጭ ጠላቶች ጋር ለመድረስ የውስጥ ጠላቶችን መደምሰስ» ፤ «የውስጥ አድኃሪ ካልተወቃ አብዮታችን ታጥቦ ጭቃ» በማለት አሻፈረኝ ብሎ በአብዮቱ ሠፈር ጸና ። የእናት አገሩንና የአብዮቱን ህልውናም በምንም ዓይነት ነጥሎ እንደማያያቸው ለማረጋገጥ «የአብዮቱን ጠላቶች ለጊዜው ተዋቸውና በእናት አገርህ ጠላቶች ላይ ዓይንህን አተኩር» የሚለውን የአድኃሪዎች መሥመር በማክሸፍ «አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት» በሚለው የትግል መፈክር ሥር ተሠለፈ

ዛሬ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ አወናባጁን መሥመር አሽቀንጥሮ ጥሎ በውስጥና በውጭ አድኃሪዎች መካከል ፤ በአብዮቱና በእናት አገሩ ክብርና ህልውና መካከል ምንም ሊነጣጠለው የማይችል ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት እንዳለ ተገንዝቧል ። ይህንንም ተገንዝቦ በውስጥና በውጭ ጠላቶቹ ላይ በአብዮቱና በእናት አገሩ ጠላቶች ላይ ለመዝመት ከዳር እስከ ዳር በአብዮታዊ ወኔ በመንቀሳቀስ ላይ ነው ።

ይህንን ዘመቻውን ተራማጆች በሙሉ ይደግፉታል ። በአድኃርያን ላይ በሙሉ ፤ በእናት አገራችን ክብርና ህልውና ጠላቶች ላይ በሙሉ የሚደረግ ዘመቻ እንደመሆኑ መጠን ፤ የኢትዮጵያ አብዮታውያን ለዚህ ዘመቻ በግንባር ቀደምነት ለመሠለፍና ለመሞት ዝግጁ ናቸው ። ይህ ዘመቻ የአብዮታችን የማይነጠል አካል እንደመሆኑም መጠን ፤ በአድኃሪው ቢሮክራሲ አማካይነት ሊካሔድ እንደማይችልም የታወቀ ነገር ነው ። በዚህ ፋንታ አብዮታውያን በሙሉ ይህ ዘመቻ አብዮታዊ አመራር ያስፈልገዋል ይላሉ ። ገና መብላላት ያለባቸው ልዩነቶች ቢኖሩም ፤ ይህን አብዮታዊ አመራር ሊሰጥ የሚችለው ማነው ? በሚለው ጥያቄ ላይ ነው ። በበኩላችን ማንም ይስጠው ማን አብዮታዊ አመራር በምንም ዓይነት የማያሻማ ይዘት አለው ። በሱ ላይ አስቀድሞ ግልጽ የሆነ አቋም መያዝ ያስፈልጋል ።

በአጭር አነጋገር ፤ አብዮታዊ አመራር ማለት በአሁኑ ወቅት አገራችንን ከየአቅጣጫው ቀስፈው የያዟት ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት ፤ በአብዮቱ መግፋትና በአብዮቱ ድል ማድረግ ብቻ ነው ብሎ የሚያምን አመራር ነው ። አብዮታችን ካልገፋ ያሉንን ችግሮች በምንም ዓይነት ልናቃልላቸው አንችልም ። አብዮታችን ካልገፋ ምንጊዜም ከድጡ ወደማጡ እየገባን ከችግር ችግር እየተዋጥን እንሔዳለን ። አብዮታችን ከገፋ ግን ከሱው ጋር በጥብቅ የተያያዙት የብሔራዊ አንድነታችን ፤ የብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችን ችግሮችም አብረው ይፈታሉ ።

አብዮታዊ አመራር ከዚህ ችግር ለመውጣት አብዮቱን ወደፊት ማራመድ ያስፈልጋል ብሎ ካመነ ዘንድ ፤ በአድኃሪው ቢሮክራሲ ላይ ፋታ የማይሰጥ ዘመቻ ማድረግ ይኖርበታል ። አብዮቱ ሊገፋ የሚችለው በሰፊው ሕዝብ የነቃ ፤ የተደራጀና የታጠቀ ተሳትፎ ከዕለት ዕለት ማደግ ጋር ተያይዞ ነው ። ለዚህም ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ መለቀቅ ፤ ሕዝባዊ ድርጅቶች በያሉበት እንዲያብቡ ማድረግ ፤ ከየካቲት ወዲህ የፈለቁት አዳዲስ ሕዝባዊ አካሎች እንዲፋፉ ማገዝ ፤ ወደአጥቂነት የተሸጋገረው አብዮታችን ማጥቃቱን እንዲቀጥል ሰፊውን ሕዝብ ማስታጠቅ ፤ ማደራጀት ፤ አሁንም ማስታጠቅ ማደራጀት ፤ ስለአብዮቱ ሒደት አገራችንን ስላሉባት ችግሮች ያልተድበሰበሱ ገለጣዎችንና ሴሚናሮችን በያለበት ማፋፋም ፤ የውይይት ክበቦችን ዲሞክራሲ ማጠናከር ፤ ለዚህ ሁሉ ወጣት ካድሬዎችን አሁን ካለው ቍጥር እጥፍ ድርብ አድርጎ በአገሪቱ ማሠማራት . . . ያስፈልጋል ። አብዮታዊ አመራር ይኸንን ያደርጋል ። በፀረ—አብዮት ኃይሎች ተከበን ፤ ከውስጥ ስንት አሻጥር እየተሠራብን ፤ የአገራችን አንድነትና ህልውና እንደዚህ ተደፍሮ እንዴት በአሁኑ ጊዜ «ዲሞክራሲ» ፤ «የውስጥ ትግል ይፋፋም» . . . ወዘተ ይባላል ? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል ። መልሱ በጣም አጭር ነው ። በአሁኑ ጊዜ ያሉብን ችግሮች እጅግ ሥር የሰደዱ ከመሆናቸው የተነሣ ፤ በምንም ዓይነት ቢሆን ያለሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ሊፈቱ አይቻልም ። ሰፊው ሕዝብ ደግሞ ሳይነቃ ፤ ሳይደራጅና ሳይታጠቅ የረባ ተሳትፎ ሊያበረክት አይችልም ። ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ የአብዮታችንም መግፋት የአብዮታዊት እናት አገራችንም ህልውና መረጋገጥ አይችልም ። ስለዚህ ነው ዛሬ ለአብዮቱና ለእናት አገሩ የተነሣ አብዮታዊ ዜጋ ሁሉ ካሉብን ችግሮች ሁሉ ለመወጣት አብዮታችን ይግፋ በማለት ለመታገል፤ለመሠዋትና ድል ለማድረግ መነሣት ያለበት።

አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት !

የነቃ ፤ የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ ዓመፅ ያሸንፋል ።